


አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ፍትህ መቼ? አሁን! እኩልነት መቼ? አሁን! ወንድማማችነት መቼ? አሁን! የማሰብ፤ የመጻፍ የመናገር መብት መቼ? አሁን! አንድነት መቼ? አሁን! ነፃነት መቼ? አሁን! እድገት መቼ? አሁን! ሠላም መቼ? አሁን! ......................መቼ? አሁን! መቼ? አሁን! መቼ? አሁን!

አሁኑኑ! አሁኑኑ!........................አሁኑኑ!
ጊዜ የለም፤ ፀሐይዋ እያዘቀዘቀች ነው! **ጀንበር ሳይጠልቅ መፍትሔ ይፍለቅ!**
ወያኔ መንፈራገጡን ትቶ፤ ሳይመሽ ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጡ የሕዝብ ባለ አደራዎች አስረክቦ አሁኑኑ ቦታውን መልቀቅ ይኖርብርታል::
ከአሁን ካለፈ ይመሻል፤ ከመሸ የሚከተለው ድቅድቅ ጨለማ ነው፤ ጨለማ ደግሞ ለባለጌና ለሌባ እንጂ አገሩን ለሚያፈቅር ጨዋና ታማኝ ሕዝብ፤ አይበጅም ::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲን ከወያኔ (ኢህአዴግ) በምጽዋት የሚቀበል፤ አካለ ስንኩል ፍጡር: ወይም ዜጋ ሳይሆን፤ በትግሉ ውጤት ከወያኔ እጅ በግድ ፈልቅቆ የሚጎናጸፈው የጀግንነት ምሱ መሆን አለበት :: አምባ ገነኖች ምንጊዜም ሥልጣን ለሕዝብ በፈቃዳቸው ያስረከቡበት ጊዜ ስለሌለ፤ ዲሞክራሲን በምጽዋት መልክ ከወያኔ የሚጠብቅ

ግለሰብ፤ ወይም ቡድን፤ ወይም ማህረሰብ፤ ወይም የፖለቲካ ድርጅት፤........ወዘተ ካለ እሱ በታሪክ ገለባ ውስጥ ተደብቆ: ገለባው ሲቃጠል አብሮ የሚነድ ሰነፍ ፍጡር ነው ::

ወያኔዎች በአቶ በመለስ ዜናዊ መሞትና አለመሞት ጉዳይ፤ እየተወኑ ያሉት ተራ ተውኔት ከራሳቸው በስተቀር የሚያታልለው (የሚያዘናጋው) ዜጋ አይኖርም፤ « ጫጩት ፊት ፈንግል አይወራም » እንዲሉ፤ የህወሃት የመጀመሪያ ቀለበት ቱባ ቱባ ባለስልጣናት፤ ኢህአዴግ በሚል ስም የፈለፈሏቸውን ተለጣፊ ድርጅቶች በሙሉ ወደ ጎን አግልለው: መለስ ዜናዊን እኔ ልተካ፤ እኔ ልተካ፤ እያሉ ይሻኮታሉ::
ተለጣፊ ድርጅቶቹም አፋቸውን ተለጉመው፤ ዝንባቸውን እሽሽ....... እያሉ ጌቶቻቸው የሚወስኑላቸውን ከዳር ቆመው፤ ይጠባበቃሉ፤ አይምሯቸው የነጠፈ በመሆኑ፤ ከነሱ ጭንቅላት የሚፈልቅ ይህ ነው የሚባል ቁነገር የለም፤ ለሆዳቸው እንጂ ለህሊናቸው ማደር ካቆሙ ይኸው 21 ዓመታት አለፈ፤ አሁንም ያው ናቸው አልተማሩም፤ አይማሩም መማርም አይፈልጉም ::

ከተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ማህበራትና፤ እንዲሁም ከአንዳንድ ግለሰቦች ሰሞኑን የምንሰማው እሰጥ አገባ፤

- ሕገ መንግሥቱ ክፍተት አለው፤
- ሕገ መንግሥቱ ግልጽ አላደረገም፤
- ሕገ መንግሥቱ ጎደሎ ነው፤...........ወዘተ የሚሉ ክርክሮች ሲሆኑ፤ እስቲ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥቂት ጥያቄዎችን እያነሳን እናጢን፤

- ሕገ መንግሥቱን ማን አወጣው ?
- ሕገ መንግሥቱ ለምን ጎደሎ እንዲሆን ተፈለገ ?
- ሕገ መንግሥቱን ማን መከረበት ?
- ሕገ መንግሥቱን ማን ተቸው ?
- ሕገ መንግሥቱን ማን አጸደቀው ?
- ሕገ መንግሥቱን ማን እንዲያከብረው ይገደዳል ወይም ይፈለጋል ?
- ሕገ መንግሥቱን እነ ማን አያከብሩትም ?
- እነማን ከሕገ መንግሥቱ በላይ ናቸው ?... ?... ?... ?ወዘተ

ሕገ መንድሥቱ: በ ህወሃት ለ ህወሃት፤ አሁንም በ ህወሃት ለ ህወሃት፤ ረጅም የሥልጣን ዘመን እንዲያመች ተደርጎ፤ በእራሱና በራሱ መልክ ጠፍጥፎ በፈጠራቸው ተለጣፊ ድርጅቶቹ፤ የረቀቀ፤ የጸደቀና የታወጀ፤ በመሆኑ: ጎደሎ መሆን እንዴት ይነሰው?!

በራሱና በአምሳያ ተለጣፊ ድርጅቶቹ የረቀቀና የጸደቀ በመሆኑ ለሕገ መንግሥቱ ጎደሎነት፤ ወይም ክፍተት ወይም ሽፍጥ በሉት፤ ተጠያቂው አሁንም እራሱ ህውሃት ወይም ወያኔ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ: ትምክህተኛ፣ ኢሠፓ፣ የጥንት ሥርአት ናፋቂ፣ ኢህአፓ.......ወዘተ እየተባለ፣ በየምክንያቱ ወደጎን ተገፍቶ፣ እነሱው አብኩተው፣ እነሱው ጠፍጥፈው ለነሱ በሚያመች መልክ፣ የጋገሩትን ሕገ መንግሥት፣ ያ ወደጎን ገፍተው የጣሉት ሕዝብ እንዲያከብርላቸውና እንዲቀጣበት ያወጡት ሲሆን፣ እነሱ ግን ከህግ በላይ በመሆናቸው፣ ያወጡትን ሕግ እንኳን የማክበር ግዴታ የለባቸውም::
የድሃ አንገት የምታንቅ፣ ቀጭን ሕግ ይሏችኋል ይች ናት!

ሰፊው ሕዝብ ይፈለግ የነበረው፣ እነሱ የሚጭኑበትን ግብር ለመክፈልና፣ በጥጋብ ጠርነት ሲያውጁ እየሄደ ተማግዶ እንዲሞት ብቻ ነበር፣ አሁንም እየሆነ ያለው ይኸው ነው:: ይህ ተንኮላቸው በባድመ፣ በሱማሌና በሱዳን ተፈጽሟል: አሁንም የሕዝብን የለውጥ ፍላጎት፣ አቅጣጫ ለማስቀየር፣ ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ሊጠቀሙበት ቢዳዳቸው፣ የሕዝብ ድጋፍ ስሌላቸው ሽንፈታቸው አይቀሬ ነው ::

ለዚህ ነው አሸባሪ፣ የሻቢያ ተላላኪ፣ (ለሻቢያ ተላላኪነት ከህወሃት በላይ ማን ነበረና?!) ነጭ ለባሽ፣ የሃይማኖት አክራሪ..... ወዘተ እያሉ ሠላማዊውን ሕዝብ እያመሱ ያሉት፣ ስለዚህ ጠንቀቅ ማለት ያሻል !!

ህገ መንግሥቱ ጎደሎ እንዲሆን ተፈልጎ ለመቀረጹ ማስረጃ የሚሆነው፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስተር ተብለው የተሰየሙት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ፣ በሕገ መንግሥቱ መሠረት አቶ መለስ ዜናዊን ተክተው መሥራት ሲገባቸው (ያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁንታ ካገኙ) ከወርቅ ተብዬው ጎሳ ባለመሆናቸውና: የይስሙላ (በአራዳ ልጅ አባባል የቁጩ) ምክትል ጠ/ ሚንስትር ስለሆኑ፣ እንደ አሮጌ ቁና ወደ ጎን ተጥለው፣ የህወሃት ወይም የወርቁ ጎሳ አባላት፣ ቀን: ቀን: ለማስመሰል ትከሻ ለትካሻ ቢተሻሹም፣ ማታ:ማታ: አንዱ ሌላውን ዘንጥሎ፣ አቶ መለስን ተክቶ ስልጣን ላይ ጉብ ለማለት ድብብቆሽ ይጫወታሉ:: ታድያ የኢትዮጵያ ሕዝብ የነዚህ ተኩላዎች ጫካ ሆኖ እስከመቼ ድረስ ይኖራል?

የወያኔ ወይም የህወሃት መሪዎች እጅግ አሳፋሪው ሥራ፣ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በሕገ መንግሥቱ መሠረት፣ የጠቅላይ ሚንስትርነት ሥልጣኑን ተክተው እንዳይሠሩ፣ መገደቡ ወይም መከልከሉ ሲሆን፣ በነሱ አጠራር ለደቡብ ሕዝቦች፣ በእኔ አጠራር ለኢሉባቡር፣ ለጋምጎፋ፣ ለሲዳሞ፣ ለባሌና............ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ትልቅ ንቀትና ስድብ ከመሆኑም በላይ ወደ ሁለተኛ ዜጋነት ዝቅ እንደማድረግ ይቆጠራል::

የህወሃት ባለስልጣናት፣ ጊዜ ለመግዣ የሚያደርጉትን አጉል ውዥንብር ትተው፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብ ፈቃድ ተገዢ በመሆን፣ ሥልጣን ለሕዝብ አስረክበው የሠላም እንቅልፍ ቢያንቀላፉ ይመረጣል::

ይኸንን በማድረጋቸው ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርታና ፍቅር ይቸራቸዋል እንጂ እነሱ እንዳደረጉት ለቂምና ለበቀል አይዳርጋቸውም፣ እነሱም የሚያጡት ነገር አይኖር:: በተቃራኒው በስልጣን ላይ እንደ ሙጫ መጣበቅ የሚያመጣው ጠንቅ ለራሳቸው፣ ለአገርና ለወገንም ስለማይበጅ፣ ቢያስቡበት መልካም ነው ::

**በአንዱ ሁሉም፤ በሁሉም አንዱ ይድናል፤ በአንዱ ውስጥ ሁሉም፤ በሁሉም ውስጥ አንዱ አለና!** ለአገርና ለሕዝብ ስትሉ ልቦና ግዙ፤ ይህንን በማድረጋችሁ እንደሸንፈት አትቁጠሩት፤ ይልቅስ ትልቁ ሸንፈት ከሕዝብ ለመቀላቀል የተፈጠረውን አጋጣሚ አለመጠቀም ነው ::

- *“ Chance knocks only once but never twice ! ”*
*« ዕድል አንዴ እንጂ ሁለቴ በር አታንኳኳምና! » ተጠቀሙበት*

- *« Qui peut arreter la haine seul l’amour »*
*Léonard devinci*

*« ጥላቻን የምታቆም ብትኖር ፍቅር ብቻ ናት »*
*ሌዎናርዶ ዳቪንቺ*

እናም ከልባችሁ የሕዝብ ፍቅር እንጂ ጥላቻ አይፍለቅ!!

ከአሁን በኋላ ማንም የማይገለልባት፤ የአንድ ጎሳ የበያይነት ያልሰፈነባት፤ ማንም ከማንም በታች፤ ማንም ከማንም በላይ የማይሆንባት፤ የዕኩልነትና የጋራ አገር፤ የጋራ ቤታችንና መጠለያችን የሆነች አዲሲቷን ኢትዮጵያ በጋራ አብረም መመሥረት ይኖርብናል፤ ይህን በማድረጋችን ሁላችንም እንድናላን፤ ይህን ባላማድረጋችን ግን ሁላችንም አብረን እንጠፋለን::

የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ የተነጠቀ ድሉን መረከብ ያለበት ሳይዘገይ አሁኑኑ ነው! የለውጥ ፈላገው ክፍልና፤ ሰፊው ሕዝብ፤ ሊያስብበትና ሊዘጋጅበት የሚገባው፤ እንደ ህወሃት አባላት፤ መለስ ዜናዊን ማን ይተካቸዋል? ሕገ መንግሥቱ ክፍተት አለው፤ ሕገ መንግሥቱ ጎደሎ ነው፤ ሕገ መንግሥቱ ግልጽ አይደለም የሚለው ሳይሆን: ይህ አምባ ገነን፤ ዘረኛ፤ አድኋዊ ከፋፋይና ፍትህ ደፍጣጭ፤ ሥርአት እንዴት ለሕዝብ ፈቃድ ተገዢ በሆነ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርአት ይተካል? የሚለው መሆን አለበት::
ነገ ሌላ ቀን ነው: የራሱ ጥሪ፤ የራሱ ሂደት፤ የራሱ ታሪክ አለውና !!

ነሃሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም. (August 8/2012)

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!
ኢትዮጵያ በተባበሩ ልጆቿ ክንድ ተከብራ ለዘላለም ትኑር !!